የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 50
ADDIS ABABA 15th July, 2013

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፩/፪ሺ፭ ዓ.ም

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ (ማሻሻያ) አዋጅ ...ገጽ ፮ሺ፱፻፯

CONTENTS

Proclamation No. 801/2013

Commercial Registration and Business Licensing (Amendment) Proclamation ............ Page 6907

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፩/፪ሺ፭

## የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፮/፪ሺ፩ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የንግድ ምዝገባና ፈቃድ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፰፻፩/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ማሻሻያ**

የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፮/፪ሺ፩ (በአዋጅ ቁጥር ፯፻፴፩/፪ሺ፬ እንደተሻሻለ) እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተተክቷል፡-

"፮/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በስራ ላይ በነበሩት ሕጎች መሠረት በንግድ መዝገብ ተመዝግቦም ሆነ ሳይመዘገብ በማናቸውም መንግሥታዊ አካል ፈቃድ ተሰጥቶት የንግድ ሥራ የሚሠራ ማንኛውም ሰው አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በ ፲፪ ወራት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት በንግድ መዝገብ መመዝገብ ይኖርበታል፤ ሆኖም ሚኒስቴሩ ከኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ወይም ክርክሮችን በመዳኘት

## PROCLAMATION No. 801/2013

## A PROCLAMATION TO AMEND THE COMMERCIAL REGISTRATION AND BUSINESS LICENSING PROCLAMATION

WHEREAS, it has became necessary to amend the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 686/2010;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Commercial Registration and Business Licensing (Amendment) Proclamation No. 801/2013".

**2. Amendment**

The Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 686/2010 (as amended by Proclamation No. 731/2012) is further amended as follows:

1/ sub-article (6) of Article 6 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (6):

"6/ Any person who, whether registered or not registered in the commercial register in accordance with the laws which were in force prior to the coming into force of this Proclamation, has been carrying on a commercial activity under a license from any government body, shall be registered within 12 months from the effective date of this Proclamation; provided, however, that the Ministry may undertake registration

ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.30

ምክንያት ወይም በሌሎች ተገቢ ናቸው ብሎ በሚያምንባቸው ምክንያቶች በተጠቀሰው የ፲፪ ወራት ጊዜ ውስጥ ያልተመዘገቡትን በሚመለከት ምዝገባ ሊያከናውን ይችላል።"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተተክቷል፡-

"፯/ ለንግድ ሥራ የሚጠቀምበት ቤት የራሱ ከሆነ የባለይዞታነት ካርታ ወይም የኪራይ ከሆነ በሰነድ አረጋጋጭ የተረጋገጠ የኪራይ ውል ወይም ይህንን ማቅረብ ካልቻለ ስለቤቱ አድራሻ ከአካባቢው የመስተዳድር አካል የተሰጠ የጽሑፍ ማረጋገጫ።"

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

"፩ የንግድ ምዝገባ እድሳት ምዝገባው የተከናወነበት ወይም የታደሰበት የበጀት ዓመት ካበቃ በኋላ ባለው የበጀት ዓመት ውስጥ ለበጀት ዓመቱ ወይም ለወደፊቱ አምስት የበጀት ዓመታት በአንድ ጊዜ መከናወን አለበት።"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተተክቷል፡-

"፭/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የላኪነት ወይም የአስመጪነት የንግድ ፈቃድ ሲሰጥ በንግድ ፈቃዱ ላይ የንግድ ሥራ መስኩ ወይም መደቡ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር ፈቃዱ በሥራ ላይ ሊውል አይችልም።"

## ፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

፩/ ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪(፩) የተመለከተው ማሻሻያ ከሐምሌ ፲፯ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ጀምሮ ዘግይተው ለተከናወኑ ምዝገባዎችም ተፈጻሚ ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

in cases where in relation to investment projects or due to adjudication of disputes or due to other cases deemed appropriate by the Ministry the registration has not been made within the 12 months period."

2/ sub-article (7) of Article 10 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (7):

"7/ the title deed of his business premises, if he owns it, or the authenticated contract of lease, if it is leased, or where such requirements could not be fulfilled, a written verification of its address from the local administration."

3/ sub-article (1) of Article 18 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ Renewal of commercial registration shall be made for every budget year or for the future five budget years altogether, within the budget year following the expiry of the period of registration or renewal."

4/ sub-article (5) of Article 30 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (5):

"5/ An export or import license may not be validly used unless the business category or type is clearly indicated in the license when it is issued by the Ministry pursuant to sub-article (2) of this Article."

## 3. Effective Date

1/ This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the amendment made under Article 2(1) of this Proclamation shall be applicable to late registrations conducted after the 24th day of July, 2012.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of July , 2013.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ